# ተስቦ ተነሳ

አገሬ ከስዊድን ሐምሌ 2011

ተስቦ ተነሳ፤  ብለን እሹሩሩ
መርዛማው ጎጠኛ፤  ከነስራስሩ
ጥፋት እንደሆነ፤  ቀርቶ መጠርጠሩ።
        እያልን እሹሩሩ፤  በህብረት ሆነን
        የዘር መርዝ የያዘ፤  ገንጣይ አነሳን።
እሱ እንደለመደው፤  ገንጣይ አዝሎ መዞር
አሸከመንና፤  ጫናው ሆነ በአገር።
        አርባ አመት የሞላው፤  ያልጠና ጎልማሳ
        በጀርባዬ አሳፍሮ፤ ሊያሳየኝ አበሳ !
አንቀልባ አቀብሎ፤   ማዘያ ለገንጣይ
ተስቦን አስቦ፤  በአገር በወገን ላይ
ወዶ ገባው ሁሉ፤  መጠቃቱን ሳያይ
አጥፊውን የጎጥ መርዝ፤  ይዟል በጀርባው ለይ።
        ድርጊቱ ከባድ ነው፤  ሰላም የሚነሳ
        እራሱን የማይችል፤ የአርባ አመት ኮሳሳ
        በወገን ላይ ጭነት፤  አንስቶ የሳንሳ
        መርዘኛው ጎጠኛ፤  ተስቦ ተነሳ።
አወይ መከረኛው፤  የአገር ልጅ ወገኔ
አልቻልኩም እንዳይል፤ በማጣቱ ወኔ
        ይሁንም እንዳይል፤  ጥፋት ሆነ በእሱ
        ህሊና ሲወቅሰው፤  ሲታረቅ ከራሱ።
እተዳደር ብሎ፤  በሳቅ በጨዋታ
 ይህን ኑሮ ብሎት፤  የፈራዉ ይሉኝታ
ጠፍቶ ማጥፋቱ ነው፤ የማታ የማታ
በዘሩ ተስቦ፤   ተለክፎ ሲረታ።
        መኖር የሚያስፈራው፤ ከገንጣይ ተጣልቶ
        በጀርባው አንግቦ፤  ማጥፋቱ ነዉ ሞቶ።
አዝሎትም  እንዳይዞር ፤ ጀርባው ተላላጠ
ውስጥ አካሉን በላው ፤ እየቆጠቆጠ
ተስቦ ነውና ፤ በዘር የቀለጠ ።
        ዘመድ አዝማዶቹም ፤ በእሱ ተሳለቁ
        ከሰው ተራ ወጣ ፤ ስላልሆነ ብቁ
        ሸሹ ተጠየፉ ፤ በገና በሩቁ ።
እንዲህ አይነት ሸክም ፤ እንዲህ ያለ ስራ
እየወደቀብን ፤  በተራ በተራ

EthioLion.Com

ለራስ የማይጠቅም ፤ ወገን አያኮራ
ተዋርዶ ማዋረድ ፤ በአገር ላይ መከራ
        አጥፍቶ እሚጠፋ ፤ ገንጣይ አዝሎ ጉዞ
        በጀርባ ታዝዞ ፤ የዘር መርዙን ይዞ
ከነምናምንቴው ፤ ሳይፀዳ ሳይድን
ተስቦ ሲነሳ ፤ ወይኔ ምን ልሁን ።

EthioLion.Com